
# አማራዎች እየተገደሉ 'ኩላሊታቸው ጉበታቸውና የታፋቸው ሥጋ እየተቆረጠ ተጠብሶ በጉምዞች ሲበላ! ጋዜጠኞች፤ አማራ ወጣቶች፤ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችና ምሁራን ዝምታን ለምን መረጡ?

**ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ)**

**8/24/2015**




ያለፈው "በሻዕቢያ መጠቃታችንን ለማስረሳት የተመለመሉ ነገረፈጂ/ ሎቢስቶች" በሚል ያቀረብኩት የመነጋጋሪያ ጽሑፌ ላይ ኢትዮጵያ በሻዕቢያ በወያኔ እና በኦነግ መሬት ተጥላ ስትደበደብ የሚያሳየው የካርቱን ስዕል በስሕተት ከአሌፍ መጽሔት የተገኘ ብየ ነበር። በኋላ እቤት ሄጄ ማሕደሬን ስመረምረው ግን አሌፍ ሳይሆን "ኢትዮጵያን ረቪው" በመጀመሪያ አካባቢ እትሙ በካርቱን ገጽ

አምድ ላይ ያወጣው ስለሆነ ለወቅቱ የኢትዮጵያን ሪቪው መጽሔት አዘጋጆችን አመሰግናለሁ።

ከላይ የሚታየው ይህ ካርቱን ደግሞ ሙዳይ መጽሔት ያተመው ነው። ሰዓሊውም ገጣሚውም በካርቱኑ ላይ ይታያል። ስለዚህም ለሙዳይ መጽሔት አዘጋጆች አመሰግናለሁ።

ይህ ለዛሬ ለመነጋገሪያ የመረጥኩት ዜና እጅግ አስደንጋጭ እና "መሐረነ ክርስቶስ" የሚያሰኝ በመሆኑ ርዕስ ለመምረጥ እጅግ ተቸግሬአለሁ። ዜናውን ለሕዝብ ይፋ ያደረገው "እግዚአብሔር ይባርካከው፤ዕድሜ ሰጥቶ ያጠንክረው" ሞረሽ ወገኔ የተባለው ስለ አማራ ወገኑ የቆመ ድርጅት ይህ ዜና ይፋ ሲያደረግ የክስተቱ አዲስነት እና ዘግናኝ ጭካኔነት ለመግለጽ እንደኔው ቃላት አጥቶ በምን ቃላት መግለጽ እንደሚችል በዜናው ዘግቦታል።

ወደ እኔው ሐተታ ከመዝለቃችን በፊት፤ ሞረሽ ዘገባውን እንዲህ ይላል፤

"በዐማሮች ላይ የተፈፀመ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ልዩ ዘገባ ቅፅ ፫፣ ቁጥር ፩" ካለ በሗላ፤ የዜናው ዘግናኝነት አጅግ ከባድ በመሆኑ ለመስማትም ሆነ ዜናውን ለሕዝብ ለማስተላለፍ አንዴት "በምን ቋንቋ እንግለጸው!?

ሰውን ሰው በላው!

ጉምዞች ዐማሮችን አርደው በሏቸው! ምንስ ብንል፤በምንስ ቋንቋ ቢገለጽ ዜናው ለጀሮ ማስሰማት ይቻላል?" ሲል እንደተቸገረ በዜናው መግቢያ ጭንቀቱን ገልጿል።

ይህ ጉድ፤ ይህ መሐረነ ክርስቶስ የሚያሰኝ ሰውን ሰው የመብላት ዜና ለኢትዮጵያዊያን ከባሕል፤ከሃይማኖት፤ከሞራል እና ከሰብአዊነት ተግባር እጅግ ሰምተነው የማናወቅ በመሆኑ ከሞረሽ ዘገባ መረዳት ትችላላችሁ።

ሰው ሰውን አርዶ የሰው ሥጋ ሲበላ የተያዘ በዘመነ አጼ ዮሐንስ ዓድዋ ከተማ ውስጥ እንደነበር የዘመኑ ዘጋቢዎች ዘግበውታል። ንጉሡም ባራጁ ሰውዬ ላይ የሞት ቅጣት በሕዝብ ፊት እንዲፈጸም አድርገው ተቀጥቷል። ታሪኩም አምና በዝርዝር አቅርቤው እንደነበር ትዝ ይለኛል።

ያ ክስተትና ድርጊት ከባድ ርሃብ በመግባቱ፤የሚበላ በማጣቱ እንደሆነ የዘመኑ ዘጋቢዎች ገልጸውታል። በዚህ ወር (ኦገስት 2015/ነሐሴ 2007) ይህ በቤንሻንጉል ጉምዝ የተፈጸመው የ240 አማራዎች ነብስ በጥላቻ ተጨፍጭፎ ጉበታቸው እና ሥጋቸው በእሳት እየተጠበሰ በጉሙዞች የመበላት ዜና ዘገባ ግን ድርጊቱ ወያኔ ያቀነባባረውና ፖሊሲው በአማራ ሕዝብ ላይ የዘር ጽዳት እንዲፈጸም ትግሉን ሃ ብሎ ሲጀምር እስካሁን ድረስ እየፈጸመው ያለው ያላቆመው የአማራን ዘር የማጥፋት ወንጀል ለዘግናኙ ድርጊት መነሻ ምክንያት ስለሆነ፤ ይህ ክስተት በአፄው ዘምንም ሆነ በሌቹ ዘመነ ነገሥታት ተደረገ ከተባለው ወንጀል እና ድርጊት የተለየ ነው።

ሞረሽ ዜናውን ሲያቀርብ ለአማራው ሕብረተሰብ (በእኔ ግምት ወላጆቻቸውን የከዱ አማራ ወጣቶችን እና ምሁራንን ጥሪውን አይጨምርም፤ ምክንያቱም የስቃዩ ተጨማሪ ተባባሪዎችና አስረዛሚዎቹ እነሱ ናቸው እና) እንዲህ ይላል፤

«ኢትዮጵያ» በሚባል ሠፊ ውቅያኖስ ውስጥ ሆነህ፣ አብሮህ የሚርመሰመሰው ሻርክ እና ዓሣ ነባሪው ቆርጥሞ እየጨረሰህ ነው። በአሁኑ ዘመን ውቅናኖሱ ውስጥ ያሉት «ሁሉም ፍጥረቶች» በሚባልበት ደረጃ ያንተ ጠላቶች ሆነዋል። በሠፊው ውቅያኖስ ውስጥ በሰላም መኖር የምትችለው በውስጡ የሚኖሩት ፍጥረቶች ሁሉ ያንተን ኀልውና አውቀው እንደነሱ የመኖር መብትህን ሲያከብሩልህ ብቻ ነው። ይህን ማረጋገጫ የምታገኘው ደግሞ በመፍራት እና በመሸሽ ሳይሆን፣ ተደራጅተህ መብትህን እና ጥቅምህን ለማስከበር ዝግጁ ስትሆን ነው። ተደራጅተህ በቡድን እና በተናጠል የሚያጠፉህን እና ሊያጠፉህ የተነሱትን «አልጠፋም! እምቢኝ! አሻፈረኝ!» ልትላቸው ይገባል። አልያ ከዚህ በፊት ከምድረ-ገፅ እንደጠፉት ነገዶች ታሪክ ብቻ ሆነህ ትቀራለህ፤ ታሪክህንም ጠብቆ የሚያቆይልህ ከተገኘ። ስለሆነም ራስህን እና ተተኪውን የዐማራ ትውልድ ለማዳን የሚደረገው ይህ ተልዕኮ ለነገ በይደር ቀጠሮ የሚያዝ አይደለም። “

ካለ በኋላ በአማራው ላይ ያለፈውን ተደጋጋሚ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ጥቃት እንደተካሄደበት ያለፈውን ጊዜ ዋቢ በማድረግ

እንዲህ ሲል ያስተውሳል፤

ባለፉት ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት በቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል በሚኖሩ ዐማሮች ላይ ጉልቆ-መሣፍርት የሌለው ግፍ ሲፈፀም ቆይቷል። በቅርብ ዓመታት እንኳን፦ በ፪ሺህ፬፣ ፪ሺህ፭ እና ፪ሺህ፮ ዓ.ም. በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዐማሮች በግፍ እና በገፍ የዘር ማጽዳት ዘመቻ ተካሂዶባቸዋል፣ በሺህዎች የሚቆጠሩት ደግሞ በዘር ማጥፋት ድርጊት በጅምላ መፈጀታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። በዐማራው ላይ ይህ ሁሉ ግፍ የሚፈጸመው በትግሬ-ወያኔ አጋፋሪነት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። የትግሬ-ወያኔዎች ባለፉት ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ፭ ሚሊዮን የማያንሱ ዐማሮችን በተለያዩ ዘዴዎች ማጥፋታቸውን የተለያዩ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና ታዋቂ ምሁራን ከራሳቸው ከወያኔዎች የመረጃ ምንጮች ላይ በመነሳት ባደረጉት ጥናት አረጋግጠዋል።.....” ይላል።

መላውን ዘግናኝ ድርጊት ወያኔ እንዴት እንዳቀነባበረውና የድርጊቱ ፈጻሚዎችም እንዴት እንዳከናወኑት ዘገባውን ለማንበብ “በትግሬ-ወያኔ አጋፋሪነት ዐማራው በመተከል ተገደለ፣ ተሰለበ፣ አልፎም ሥጋው ተበላ” በማለት ዘገበውን ዜና በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ድረገጽ http://moreshinfo.com/archives/2107 ያንብቡ።

ተደብቀው ያሉትን የድረሱልን ድምጻቸወን ለማድመጥም ሆነ የጽሁፍ ዜናውን ለማንበብ ከላይ የሰጠሑዋችሁ አድራሻ በመግባት ተረዱት።በዚህ አጋጣሚ ኢትዮፓትርዮትስ.ካም

ድረገጽ እና የእስቶክሆልም የሚገኘው የኢትዮጵያን ራዲዮ ጣቢያ አዘጋጆች እና ባልደረቦች እጅግ አመሰግናለሁ። ቃለ መጠይቁ ያከናወኑት እነሱ ናቸው።

## አሁን ወደ የኔው ሐተታ እንግባ።

በሃያ አራት አመታት ውስጥ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዐማሮች ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች በዘር ማጽዳት ዘመቻ መፈናቀላቸው ይታወቃል። ተደጋጋሚ ዜና ተስተጋብቷል። ከውስጥም ከውጭም በቂ የዜና ሽፋን አልተሰጠውም። ሠሞኑን ደግሞ ከወደ መተከል (ቤንሻንጉል-ጉሙዝ) የሰማነው የሩዋንዳው እና የላይቤሪያው ዓይነት ሰው የመብላት ክስተት የትግሬ-ወያኔ በዐማራ ሕዝብ ላይ የሚፈጽመው ተከታታይ ትራጄዲ አንድ አካል መሆኑ እሙን ነው።

ላይቤሪያ ውስጥ "ጀኔራል ባት/ጥ ኔክድ" እየተባለ የሚታወቀው የሰው ሥጋ መብላት ጅግንንትና ድፍርት ሰጥቶ ጠላትን ማሸነፍ ትችላለህ የሚል እምነት በመከተል፤ጠላቶቹን እየገደለ፤ የሰው ሥጋ በምጥሚጣ ለውሶ እየበላ ከሥሩ የነበሩት ታዳጊ ወጣት ተዋጊዎችም የሰው ሥጋ እንዲበሉ በማድረግ ፤በሰው ልጅ ታሪክ የከፋ ድርጊት ፈጻሚ ተብሎ ለላይቤሪያ ጠባሳ ታሪክ ትቶላት፤ ዛሬ ንስሃ ገብቶ የሃይማኖት ሰባኪ ሆኖ በማገልገል ይገኛል።

አገራችን ውስጥ በዘመናችን እጅግ ዘግናኝ ድርጊት ተፈጽሚል ብለን ስንጽፍበት የነበረው በእስላማዊ ኦሮሞና በተጋጋዥ መሰል ተገንጣይ

ቡድኖች የአማራዎች ብልት እና ጡት በመቁረጥ፤ የህጽናትን አንገት በቢላዋ በመገዝገዝ፤እርጉዞች ሆዳቸውን በቢላዋ ቀድዶ ሽሉን በመበጣጠስ ይደሰቱ እንደነበር የፎቶግራፎች እና የቪዲኦ ቅርጾች ለታሪክ ተቀርጸው ይገኛሉ። ይህ ሰነድ ደግሞ እዚህ በራሴ በኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ ላይ ካሁን በፊት ደጋግሜ አቅርቤዋለሁ።

የጉሙዞቹ ኢንተርሃሙዌው "ሰው በላው" ቡድን ከኦሮሞዎቹ ኢንተርሃሙዌው ተገንጣይ ተዋጊዎች ቡድን ጭካኔ እና ወንጀል ለየት የሚያደርገው፤ የጉሙዙ ኢንተርሃሙዌው ቡድን እንደላይቤሪያ የሽምቅ ተዋጊዎች ለሥልጣን ሲሉ ተቀናቃኝ የሽምቅ ክፍሎችን በመግደል ሥጋቸውን በመብላት ሳይሆን፤ ጉሞዞች በወያኔ ጎትጓችነት እና የጎሳ ክልል ሰበብ በጥላቻ ተነሳስተው የአማራዎችን ነብስ እያደኑ ገድለው ጉበታቸው፤ኩላሊታቸው እና የጭናቸው ሥጋ እየጠበሱ በጨው እና በበርበሬ እያጣቀሱ የመብላታቸው ዜና ስንሰማ በኦሮሞ ተገንጣይ ቡድኖች የተፈጸመው ኢንተርሃሙዌያዊ የወንጀል ድርጊት ይህኛው እጅግ የተለየ፤ በዘግናኝነቱ የላቀ የአራዊት ባሕሪ በሰው ልጅ ሕሊና ተከሰተበት ድርጊት ነው። ከኦሮሞቹ ወንጅል ለየት የሚያደርገው ግድያው እና ጭካኔው ሳይሆን **"አማራውን ገድለው ሥጋውን መብላታቸው"** ነው ለየት የሚያደርገው ዘግናኙ ድርጊት።

የድርጊቱ ፈጻሚዎች ጉሙዞች ቢሆኑም፤ በዐማራው ላይ ይህ ሁሉ ግፍ ተደጋጋሚ የዘር ጽዳት የሚፈጸመው በትግሬ-ወያኔ የክልል ፖሊሲ እና አበረታችነት፤ እንዲሁም እቦታው አማርን ለማጥፋት

የመደባቸው ሹሞኞቹ አጋፋሪነት እንደሆነ እንኳን ሰው ወፍ ታውቀዋለች። መረጃዎችም በገፍ ሞልተዋል።

ሞረሽ ወገኔ እንዳለው ‘የትግሬ-ወያኔዎች ባለፉት ፳፭ (ሃያ አምሥት) ዓመታት ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ፭ ሚሊዮን በላይ የማያንሱ ዐማሮችን በተለያዩ ዘዴዎች መጥፋታቸው ከወያኔዎች ከራሳቸው የፓርላማ (2 ሚሊዮን) መግለጫና ከሰብአዊ ድርጅቶች የተረጋገጠ እውነት ነው። ሰሞኑን ደግሞ 240 አማራዎች በመተከል ዞን በቤንሻንጉል ጉምዝ፤ በጉሙዞች እየተገደሉ እየተበሉ ነው የሚል ዜና ይኼው እያነበብን ነው። እድሜ ለሞረሽና ለኢትዮ-ፓትርዮትስ ስዊድን ኢትዮጵያ ራዲዮን አዘጋጆች ዜናው ይፋ ተደርጓል።

አገር ውስጥ ያሉት ጋዜጠኞችም ሆኑ፤ አገር ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ዜናውን አላሰራጩትም፤ ቢየውቁትም ሊያሰራጩትም! ቀዳሚ አጀንዳቸው “ዲሞክራሲ” እንጂ የአማራው ሕብረተስብ መጥፋትና በደል ማስተጋባት መቃወም፤ ሰላመዊ ሰልፍ ማዘጋጀት፤ ኡአታን ማስሰማት ዓለማቸው አይደለም።ስለሆነም እነሱ ስለተኙለት ወያኔ ያሻውን እየፈጸመ ይገኛል።

ይህ የዘር ማጥፋት ጥቃት ሲፈጸም፤ ምሁራን፤ ጋዜጠኞች እና በተለይ አማራ ነን የሚሉ ወጣቶች እና ክፍሎች ዝምታን ለምን መረጡ የሚለው ጥያቀዬ፤ እውጭ ያለውም ሆነ እውስጥ አገር ያለው የአማራ ማሕበረሰብ እንዲወያይበት እጋብዛለሁ።

በአጥቂዎቹ የተቀየሰ የጨዋታ ስልት ውስጥ ገብተው በዲሞክራሲ ጥያቄና ትኩረት ሰክረው ናላቸው እንዲበወዝ በመደረጉ፤ የጥቃቱ

ጥልቀት ሊገባቸው አልቻለም እና ይወያዩበታል የሚል እምነትም ሕልምም የለኝም። ለምን? 24 አመት ጋዜጠኞች ነን የሚሉን በዲሞክራሲ "የሳብቨርሲቭ ዘመቻ" ተካፋዮች ሆነው በዲሞክራሲ የመፈላሰፍ ጨዋታ ውስጥ አስገብተውታልና የአማራን የዘር ማጥፋት ወንጀል ቆዳውን አያቃጥለውም። ስለዚህ በግለት ተቆጭቶ ይንጫጫል ብየ አልገምትም።

እርግጥ ሞረሽ ዜናውን በአሲምባ. ኦርግ፤ በኢትዮፓትሪዮትስ.ካም ፤ በወልቃይት.ካም፤ በዘሃበሻ.ካም ላይ እንዲሰራጭ ልኮት ተለጥፏል። እጅግ የሚገርመው ደግሞ አንድ ወዳጄ ነገሩን ሲከታተለው ነበርና ትናንት በሌላ ጉዳይ በስልክ ስንነጋገር፤ ኢሳት የተባለው የግነቦት 7 ሚዲያ፤ በጉሙዝ የተፈጸመው ሰው በሰው በመላት ሳይሆን የዘገበው ፤በክልሉ ተከሰተ ብሎ ያወራው ሕዝቡ ስርዓቱ ላይ አመጽ አስነስቷል፤ ሲል ነበር በዜናው ያሰራጨው። ስለ አማራ በጉሙዞች መበላት ከሞረሽ እንኳ ቅጅ እና ዋቢ አድርጎ አልዘገበም።

ሌላው በቪ ኦ ኤም ቀርቦ ነበር ስለተባለ አንድ ያልተከታተልኩት የሰብአዊ መብት አሳቢ ሰው አቀረበ የተባለው ትችት፤ ወዳጄ ሲነግረኝ፤ ሞረሽ ከዘገበው ጋር ምንም ተያያዥነት የለውም፡ ሲል ወዳጄ አጫውቶኛል። እነኚህ ሚዲያዎች ፤ዋቢ አድርገው የሚጠቀሙት፤ "የኤርትራው ፕረዚዳንት ክቡር ኢሳያስ አፈወርቂ እንዲህ አሉ;.......የሱዳን ተቃዋሚ መሪ እንዲህ ሲል ዛተ... አቶ ሥዩም መስፍን እንዲህ አሉ...በማለት ዋቢ ያሚያደርገው ሌሎች ዘጋቢዎች የዘገቡትን ነው። ሞረሽ በስንት ዘዴ እና ምርመራ መረጃዎችን በጥንቃቄ በድካም እና በስንት መከራና ወጪ፤በጥቂት

አቅሙ መረጃዎችን እየቆፈረ፤ እያገኘ ለሕዝብ የሚያወጣቸው ዜናዎችን ግን ሞረሽን ዋቢ ማድረግ ወንጀል መስሎ እየታያቸው ዜናዎችን ሞረሽን ዋቢ አድርጎ ማሰራጨትን ግን ዳገት ሆኗቸዋል።

ሞረሽ የላከው ዜና በጥቂቶቹ ቢለጠፍም፤ የሚዲያዎች (ሁሉም አልወቅስም) ሚናቸውንና ባሕሪያቸውን ያልለወጡ በግልጽ የማውቃቸው እና የማወግዛቸው እኔ "የልሂቃን ተከለ ሰውነት ገመቢ ህዋሳቶች" ብየ የምጠራቸው ሚዲያዎች እና እንዲሁም ለሕዝብ ቀመናል እያሉ እየዋሹ የፖለቲካ ቡድን አቀንቃኞች የሆኑ ሚዲያዎችና እንዲሁም፤ የግንቦት 7 ዜናዎችና ተከለሰውነት ገምቢ ሚዲያዎች እና የግንቦቱ አንዳርጋቸው ጽጌ ወዳጆች የሆኑት አንዳንድ ጋዜጠኞችና የሚዲያ ባለቤቶች፤ ስለ አማራው መጨፍጨፍ ሳይሆን የሚያወሩት ሁሌም የሚያወሩትና ትኩረት የሚሰጡት ጻረ አማራው ወዳጃቸው ማንዴላቸው አንዳርጋቸው ጽጌ በወዳጆቹ በወያኔዎች ተያዘ፤ እስላሞቹ ተፈረደባቸው፤ ጦማሪያኖቹ ተለቀቁ/ታሰሩ/ለሌላ ቀን ለፍርድ ችሎት ተቀጠሩ፤ ግንቦት7 ይህን ያህል ሚሊዮን ብር ተዋጣለት፤ ጻረ አማራው የግንቦቱ ኤፍሬም ማዴቦ ከቀጣሪው ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ባንድ ጠረፔዛ ቁጭ ብሎ ተወያየ፤ እያሉ ዜናዎቻቸው ጊዜ ሳይፈጁ በየሰዓቱና በየቀኑ በተከታታይ ሲዘግቡ አንብበናል፤=

የግንቦት 7 ካልቶችን ለማስጨብጨብና ለማስጮህና በስሜት ለማስፏጨት ከኋላ መጋረጃ ተቀምጦ የነበረው ድብቁ እዮኤል ደግሞ ሰሞኑን ብቅ በማለት፤ በብርሃኑን እና በአንዳርጋቸው እግር ብቅ ያለው "ሙሉነህ እዮኤል" የተባለው ሌላው አደናጋሪ ደግሞ

ስለ የግንቦቱ ፀረ አማራው ኤፍሬም ማዴቦ አማራን እንዲዘልፍለት ከቀጠረው ከአለቃው ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር መገናኙቱ ሎስ ቬጋስ ውስጥ ተገኝቶ ንግግር አደረገ ሲሉን፤-

ከደቡብ ኢትዮጵያ ከአንደኞቹ ህዳጣን ማሕበረሰብ ተወላጅ ነው ተብሎ የሚነገርለት ይህ ግለሰብ፤ ዛሬ የግንቦት 7 ጸሐፊ፤ የድሮው የቅንጅት ዋና ጸሐፊ የነበረ አፍራሽ ሚና ከተጫወቱት 13ቱ ውስጥ ውጭ አገር በለመዚን እና በቁርጥ በአበባ ጉንጉን ሲታጀቡ ከነበሩት አንዱ የነበረው ይህ ግለሰብ በሚሊዮን አማራ ሕይውት የደረሰው የዘር /ጀነሳይድ/ ጭፍጨፋ አንስቶ አድማጮቹን ማንቃት ተጸይፎ፤ አንድ የአይጋ ድረገጽ ማይም ሰው “የአባንግ ሜቶን” “የቆዳ ጥቁረት እያነሳ በመጻፍ አሳነሰው” በማለት የግለሰብ ግብዝነትና ዘረኝነት እያጎላ ትልቅ መነጋገርያ ርዕስ አድርጎ ይዞ በሚሊዮን ያለቀና እያለቀው አለው አማራ ማሕበረሰብ አንዲት ቃል ሳያነሳ በስሜት የሚጋልቡትን ዲያስፖራ ተከታዮቹን እያስጨበጨበ መድረክ ላይ የቦተለከውን ሲዘግቡ፤-

ከሚዲያዎቹ ጋርም አብረው ከእነ .....አንዲ አንዳርግዬ.....ብርሽ.. ብርሃኑዬ,, “ቃለ አጋኖ” ጸሐፊዎቻቸው ጋር ሆነው ስለ ቡድናቸው ዜና፤አርበኝነት፤የአንዲ ፎቶ ቅብ በ35 ሺሕ ዶላር በጨረታ መሸጡ (እባካችሁ ታሪካዊ ሳቅ አትሳቁ፤ ብዙ ድንግል የዋህ ሞልቷል)፤ እንደ ማንዴላ መስዋእት ለመክፍል ያልቆረጠ በፍርሃት ቆፈን ሆኖ ተናገር ያልተባለው ሲለፈልፍ ያዳመጥነው የማንዴላ ሽታ የሌለው የማንዴላቸው “አንዲ” ማንዴላነት በመግለጫ መልክ እያናፈሱ የማሞኛ ጦርነት ተከፈተ እያሉ የውሸት ፎቶ እየለጠፉ፤ ድርጊቶች

ሳይከናወኑ ተከናወኑ እየተባለ በሰዓትታት ውስጥ እየዘገቡ ይፋ ሲያደርጉ፤ ሲያጃጅሉ፤ መሬት ቀውጢ ሲያደርጉ፤ሰልፍ ሲወጡ፤ ሲጮሁ፤ ሲፈክሩ፤የፉከራ የቀረርቶ ዜማ በየፓልቶኩ በየድረገጹ በእዬ ዩትዩቡ ለማቅራራት ግን ጊዜ አይፈጅባቸውም። ያውም እየደጋገሙ እስኪሰለቸን ድረስ ሚዲያዎቹ በግንቦት 7 እና በሻዕቢያ ወዳጅነት የተክለ ሰውነት ቀረጻ ፕሮፓጋንዳ ሞልቶ ፈሷል!

አማራው እንደ በግ ታርዶ ሥጋው እየተጠበሰ ሲበላ ግን ምሁራኖቹ እና "ቃለ አጋኖቹ" እንዲሁም የሚዲያ ባለቤቶች ኤዲተሮች/ጋዜጠኞች ነን ባዮችና አማራ ነን የሚሉ አማርኛ ተናጋሪ ወጣቶች 'ለ24' አመት የአማራ ነብስ በዘር ማጽዳት ዘመቻ ከፍተኛ ዕልቂት ሲፈጸምብት  አይተው እንዳላዩና እንዳልሰሙ በቸልተኝነት እየታለፈ የሚዲያ ሽፋን ሳይደረግለት ለ24 አመት እያዘገመ መጥቶ ወንጀለኞች የልብ ልብ ሰጥቷቸው አማራውን ከመግደል አልፈው የአማራውን ሥጋ እስከ መብላት ይኼው እዚህ ደርሰዋል።

አማራ እንዳይደራጅ በተቃዋሚነት ስም "ተቃዋሚዎች ነን" እያሉ አማራ ነን የሚሉ አሁንም ደባው ያልገባቸው በእንቅልፍ ላይ ያሉ አንዳንድ ገልቱዎች 'ሞረሽን "ኢሰፓአኮ" እያሉ ስም በማጥፋት የወያኔ ስራ እየሰሩ፤ ስም በማጥፋት ዘመቻ ገብተው፤ አማራው ሲታረድ እራሱን እንዳያደራጅ "ብትሩን እንዲጥል" እየገፋፉ በተዘዋዋሪ ፡"የሳብቨርሲቭ ተልዕኮ" (የአፍራሽ ግብረሃይል) አነፍናፊዎች ሆነው በመሰማራት ከፍተኛ የገዝጋዦቹ ፕሮፓጋንዳ አጠናክረው በመንዛት በአማራው ሕብረተሰብ ላይ የግዝገዛ ጥቃት

ተሳታፊ ሆነው የሚዲያ አስተዋጽኦ እያደረጉ የሚገኙ ግለሰቦችና ቡድኖች አሉ።

ይህ ምልክት የውጭ አገር ሴራ በሳብቨርሲብ ዘመቻ (ያለ የውጭ አገር ሰዎች ቀጥተኛ ተሳታፊነት፤ ያለመሳርያ አገርን በራሱ ሕዝብ በገዛ ራስ ማፍረስ -) "ሳብቨርሲቭ" የተሰኘው አገርን/ሕብረተሰብን የማጥቃት ሴራ በነዚህ ሰዎች ተሳታፊነት ሥራ ላይ እየዋለ እንደሆነ የምናየው ምልክት ነው። በውስጥ አገር ተዋናዮች (ተቀባይ) በውጭ አገር (ላኪ) (ቱ ወይ/Two way) የቅብብሎሽ የጠላት ተልዕኮ በመዘርጋት ፤ የሳብቨርሲቭ፤የዲሞራላይዘሽን፤የክራይሲስ እና የዲስታብለይዘሽን ስራዎች እና ክንውኖች አገር በማፍረስ ላይ ያለምንም ጥይትና የጦር መሳርያ (ያለ ጦርነት) ኢትዮጵያ እና አማራው እንዴት ማፍረስ እንደተቻለ፤ ካች አምና በነሐሴ ላይ ከአሲምባ የፓልቶክ ክፍል ተጋብዤ የሰጠሁትን ቃለ መጠይቅ በኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ ተለጥፏል፤ ያንን አድምጡ። ምን እያልኩ እንደሆነ ስታደምጡት ይገባችኋል።

አማራው ወያኔ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚውም በግዝገዛው ላይ እጁን እንዴት አስገብቶ የሴራው ተካፋይ እየሆነ እንዳለ እዛው ትገነዘባላችሁ።በክርስትና በእስልምና ስም ከውጭ የሚላክልንን የአፍራሾች ተልዕኮ ስትገነዘቡ ምን ያህል "ተቀባዮች" እንዳሉን መገንዘብ ይኖርብናል። ኦባማ የተባለው የአዲሲ ዓለም እና የባንከሮች የጥቁር ሕዝብ ጠላቶች የሆኑትን የነዚህ ሰይጣናዊ ድርጅቶች ታላላኪ እና አሽከር የሆነው ይህ የጥቁር ሕዝብ አሳፋሪ የሆነ የውሸት ፕረዚዳንት ወደ አፍሪካ (ኬኒያ እና ኢትዮጵያ)

መጥቶ ስለ ጥቂት “ግብረሰዶማዊያን” መብቶች ሲሰብክ በሚሊዮኖች ያለቀው አማራው ላይ እየደረሰ ያለው የመብት ጥሰት ቢያውቅም ኢትዮጵያን ማፍረስ፤አፍሪካን ወደ ቅጅ አዙር ማስገባት ጌቶቹ የላኩት ተልዕኮው ስለሆነ አማራው ተጠቃ አልተጠቃ ምኑም ስላልሆነ፤ በስሩ ያሰማራቸው “የሳብቨርሲቭ ዘመቻ አቀናባሪዎቹ” ከወንጀለኞቹ ጋር እስክስታ ሲደልቁ በሳቅ በደስታ በፈገግታ ቁጭ ብሎ ሲመለከት ማየት ምንኛ አሳፈሪ ስራው አሳይቶናል።የህ ግለሰብ በታሪክ የጥቁር ሕዝብ ማፈሪያ ግለሰብ ተብሎ ቢሰየም እጅግ የሚያንስ አገላለጽ ነው።

እንዲህ ይነት አፍራሽ ሃይሎች፤ ሞራለ ቢስ ናቸው። ሰውየው ሃይማኖታዊም ሆነ ዲሞክራሲያዊ የሞራል ለከትና መመሪያ የለውም። አፍአዊ ክርስትያን እንጂ እውነተኛ ክርስትያን አይደለም። ክርስትያን ቢሆን ኖሮ ፤ለፕረዚዳንትነት ሲመረጥ ለመሃላ እጁን ያስቀመጠበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እታዘዛለሁ፤እከተላለሁ፤ ብሎ ሲምል፤ በሌላ በኩል “የማለበትን መጽሐፍ ቅዱስ” ስለ ግብረሰዶማዊያን ያሰፈረው ትዕዛዝ አፍርሶ፤ ስለ ግብረሰዶማውያን መብት ማክበር ተገቢነት ለአፍሪካዊያን ሲሰብክ፤ ክርስትያን አንዳልሆነ እና የማለበትን ቅዱስ መጽሐፍ የውሸት ማሃላ እንደማለ እና ቀጣፊና አታላይ ሰው መሆኑን አስታውሱ።

ከዚህ ግለሰብ ቀደም ብሎ፤ አማራው ለጥቃት ሲጋለጥ “አቀባዮች” የሆኑት እነ ሄርመን ኮኸን “ለተቀባዮቻቸው” ለነ ሻዕቢያ እና ወያኔ እንዲሁም ለነ ኦነጎች.... አጀንዳቸውን አስረክበው፤ አማራ እንዲጠፋ አጀንዳ ዘረጉ። ይህ የሳብቨርሲቭ ክንዋኔ በዝረዝር ለመመልከት

የኔው ቃለ መጠይቅ አውዲዮው በዩቱብ ተለጥፏል ደጋግማችሁ አድምጡት። ኔን ስም ጉግል ላይ ብትጽፉ ይታያችኋል።

ዛሬ፤ ራሳችን በራሳችን የጥፋት ፈጻሚዎች እና ተቀባዮች ሆነናል። ይህ በብዛት የሚታይ አደገኛ **ራስን የመብላት/የራስን የማፍረስ** ሂደት ጠላት **በጦርነት** ከሚሰነዝረው ጥቃት እጅግ የከፋ ክንዋኔ እየፈጸምን እንገኛለን። **"በላክ ኦን ብላክ ክራይም"** እንደሚሉት ዓይነት እርስ በርሳችን እየተበላላን ነው።የተቀባይ ትርፉ ይህ ነውና! አገሩን ያልዘጋ፤ያልቆለፈ ሕዘብና መንግሥት "ተቀባይ/ረሲፒየንት" ስለሆነ፤ ለማንም አፍራሽ ይጋለጣል። ስለሆነም፤ እራቁታችን ቆመናል! ተጋልጠናል!!! በዚህ እንተማመን። ኢትዮጵያ አለች እያሉ የሚናገሩ ሰዎች፤ ሁኔታው አልገባቸውም።የለችም፤ ጠፍታለች! ካለችበት እናፈላልጋት!

ሩዋንዳ በቱሲ ላይ እልቂት ሲፈጸም፤ የዘር ጥቃት ሲፋፋም፤ የሚዲያ ክፍሎች በቂ ሽፋን ስላልሰጡት ሕዝቡ "የአዋርነስ" ጥንቃቄ ስለጎደለው፤ እየተደረገ ያለው እና ለሚመጣው አዳጋ ዝግጅት ስላላደረገ፤አደጋው 'ባልተጠበቀ የዝግታ ሂደት ተጉዞ ድንገት በመምጠቅ" ሕዝቡ ለጥቃትና ለስደት ተዳርጎ ዓለምን ያስደነገጠ እልቂት እንዴት እንደተፈፀመ አንብበናል።

ለሩዋንዳ ዕልቂት ቀንደኛ ተጠያቂው በግድያው የተሳተፉት ወንጀለኞቹ ሳሆኑ "ሚዲያዎች" ነበሩ የዕልቂት ጋባዦቹ። በጥላቻ ቅስቀሳ የተሰማሩት የጥላቻ ሚዲያዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ የኢንተርሃሙዌው ጥላቻ ቅስቀሳ ሲተላለፍ ዝምታን የመረጡ የመንግሥትና የዲሞክራሲ ለውጥ ለማድረግ "ሽምግልና/ሞደራቶር'

ሆነው ፤ የጥላቻ ቅስቀሳ ሲፈጸም ‘ዕብዶች” የሚነዙት ጥላቻ ስለሆነ፤ እነሱን ማጋለጥ ሕብረተሰቡን (ሁቱን እና ቱሲውን) ማንቃት መልሶ ነገሩን ማባባስ ነው “ዝም ብለን ለመንግሥት ለውጥ እንስበክ” ፤ እያሉ ጆሮ ሳይሰጡ ፤ ጥላቻው አግር ጥርስ አብቅሎ ዓይኑን አጉረጥርጦ፤ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ “ዝም እንበል” ሲሉ የነበሩት ጋዜጠኞች እና ምሁራን የመጀመሪያዎቹ “ተጠቂዎች/ሰለባዎች” እነሱ ነበሩ። ከዚያ ሩዋንዳ ውስጥ በቱሲ ላይ የሆነውን የምታውቁት ታሪክ ነው።

የዘር ማጽዳት ቅስቀሳ ሲካሄድ፤ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ስለ አፍሪካ ፋሺንና ስለ ማርከሲዝም መወገድ እያንኮራፉ እንቅልፋቸውን ሲለጥጡ ነበር። በጠረጴዛቸው ስር ቀስ በቀስ እየተንፏቀቀ አግር እየሰደደ በሄደበት ወቅት “የሁቱ እና የቱሲ” ጥላቻ ንትርክ፤ አዲስ አይደለም ፤ለዘመናት የቆየ ስለሆነ፤ ብዙም ትኩረት መስጠቱ ጊዜን ማባከን ነው። እያሉ እሳቱ እስኪቀጣጠል ድረስ ፤ ጆሮ አልሰጡትም ነበር። የውጭ አገር ሚዲያዎች የተሳሳተው ድምዳሜ ውስጥ ሊገቡ የቻሉት፤ አገር ውስጥ ከነበሩት አገር በቀል የሩዋንዳ ጋዜጠኞች፤ ፖለቲከኞች እና ምሁራን ነን ባዮች ሲያገኙት ከነበረው የተሳሰሳተ እይታ በመነሳት ነበር። አንዳንዶቹ አሁን አገራችን ላይ እንዳለው ሚዲያ የሳብቨርሲቩ ተዋናዮች ነበሯቸውና ጉዞው በዛው ቀጠለ።

ዓለም አቀፍ የሚባለው የመንግሥታት ማሕበር “ዩ ኤን” ቸልተኛነት ደግሞ የባሰው ለእልቂቱ አስተዋጽኦ ያደረገው ይህ ድርጅት ነበር። ቀውስ ተነስቶ ገና ብልጭ ብልጭ ሲል፤ ፀቡን ለመቆጣጠር

የተመደበው ጥቂት ሺሕ የሚያክል የድርጅቱ ወታደራዊ ሃይል መሪ የነበሩት ካናዳዊው ጀኔራል ሮሚዮ (Romeo Dallaire) ችግሩ እየተባባሰ ስለሄደ ተጨማሪ ወታደር እና መሳሪያ እንዲላክላቸው ባስቸኳይ ሲጠይቁ፤ መለስ ዜናዊ ከባድመ ጦርነት በፊት ጓዶቹ ‘ኢሳያስ ሊወረን እየተዘጋጀ ነው” ሲሉት “ነፍጠኞች የሚያወሩት የጠላ ቤት ወሬና ምኞት ነው” ብሎ ሕዝብ እንዲያልቅ እንዳደረገው ሁሉ የተባባሩት ድርጅትም የጄኔራሉን ጥያቄና ማስጠንቀቂያ “የተለመደ ብዙ ጊዜ ያደመጥነው ሲባል የነበረ ተባባበሪ የመንደር ወሬ መረጃ ሊሆን ይችላል” (የኮፊ አናንን ቃለ መጠይቅ አድምጡ) በማለት እርደታ ሳይላክ ፤ ሩዋንዳ ውስጥ “ዘግናኝ ሆሎካስት” ተፈጸመ።

በእኛ በኩልም ያለው ተመሳሳይ ቸልተኛነት እና የአማራው ደም ለ24 አመት ሰሚ አጥቶ እየደወለ እስካሁን ድረስ እንዴት ላስከፊ ጥቃት እና ነገም ከምድረ ገጽ እንዴት ለእልቂት እየተገፋ እንደሆነ እና ምሁራንም ሆኑ ያልተማሩት የኢትዮጵያ ሕብረተሰቦች “ጉዳዩን ላላማባባስ ዝም እንበል፤ ጥቂት እደግመዋለሁ **“ጥቂት”** ናላቸው የሳቱ ሰዎች ትግሬን እናጠፋለን፤ አማራን እናጠፋለን ብለው ፓልቶክ ላይ ስላወሩ አቶ ጌታቸው ረዳ ለምን ነገሩ እንደ ትልቅ ነገር እያየህ ክብደት ትሰጠዋለህ? እንዲህ የሚሉት የተማሩ አይደሉም፤ ኩታራዎች፤ወጣቶች ናቸው..ወዘተ....ወዘተ...ወዘተ... እያሉ እኔን በቃለ መጠይቅ አድማጮች ጠይቀውኛል። ቸል እንበል፤ ነገርን ማጋነነን፤ ማባባስ ሁኔታውን ያበረታታዋል፤ እያሉ ስልክ ደውለው ያነጋገሩኝ ምሁራን አሉ (ስም አልጠራም)።

ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ እንደሄደ ሁሉ ሩዋንዳ የሆነውን ኢትዮጵያ እየሆነ ያለውን ክስተት እየተደገመ መሆኑን እዚህ እንመልከት። ሩዋንዳ ውስጥ ያለቀው ሕዝብ 8 መቶ ሺህ ነው፤ አማራው ከ5 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ጠፍቷል።ኢትዮጵያ ውስጥ በወያኔ አስተዳዳር እና ዘመን!!! ለምን እንዲህ ተከሰተ? ተዋናዮቹ እነማን ናቸው? ወያኔ ብቻ ነው? ተቃዋሚስ፤ጋዜጠኞችስ፤ ምሁራኖችስ፤ ወጣቶችስ ይህ ሁሉ ሲደረግ ምን እየሰሩ ለ24 አመት በቸልተኝነት ተቀመጡ? ለምን" የሚሉ ጥያቄዎች እንመልሳቸው።

ሩዋንዳ ውስጥ በሁቱ እና በቱሲ መካካል ጥላቻ ሲቀሰቀስ 'ቀስ በቀስ' እያለ ያፈጠጠው ፀብ፤ የውጭ አገር ሰዎች እና ቅኝ ገዢዎች የተከሉት የሳብቨርሲቭ/አፍራሾች የበጠበጡት የመርዝ ብልቃጥ እንደሆነ ታወቋል። ኢትዮጵያ ውስጥ...አረብ፤ቱርክ፤ጣሊያን አሜሪካ፤እንግሊዝ፤ሶቭየቶች.. ዛሬ ደግሞ ከላይ ተጠቀሱት ላኪዎች የተላከው ሴራ "ወያኔ እና ሻዕቢያ" ተቀባይ ሆነው በቱ ወይ/Two way/ ሃዲድ {በላኪ እና አስመጪ/ረሲፕሮካል} ተጉዘው አድርግልኝ ላድርግልህ፤ እየተለዋወጡ በአማራው ላይ ለ40 አመታት አህል የጥላቻ ቅስቀሳ በመንዛት ለእልቂት ዳርገውታል። ዕልቂቱ ሲከናወን አማራ ሰው ሆድ ዕቃው ተቀዷል፤ ራስ ቅል ተፈጥፍጧል፤ብልት ፤ ጡት ተቆርጧል፤አማራዎች በየቤታቸው እሳት ተለኩሶባቸው ወደ 13 ሺሕ የሚያክሉ በእሳት ቃጠሎ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል። ተማሪዎች ሲማሩበት የነበረውን ክፍል ተቆልፎባቸው ቤንዚን ተርከፍክፎባቸው ተቃጥለው ሞተዋል። በማቼት በቢላዋ በጠመንጃ ወዘተ ወዘተ.....የአማራዎች ደም ምድሩን አጨቅይቶታል።ወደ አገራችሁ ውጡ የሚል መፈክር ተደርጎ የዘር ጽዳት

ተፈፅሞባቸዋል። የጥላቻ ራዲዮኖች በውስጥም በውጭም አሉ፤ ዛሬም ምንም የሕግ ፍራቻ ሳያግዳቸው፤ በአማራ ሕብረተሰብ ላይ የጥላቻ ቅስቀሳቸው እየቀጠሉ ያሉ ኢትዮጵያዊ ኢንተርሃሙዌይ ቡድኖች አሉ።ይህ ሁሉ ሲሆን ኢትዮጵያዊያን እንዴት ቻል ብለው ዛሬም ምንም ኮሽታ ሳያሰሙ ዝምታን መረጡ?

መልሱ ቀላል ነው።፡ሰላምን እና ወንድማማችንትን ለማስፍን የቆሙት ሚዲያ ተብየዎች የችግሩ ክፋት እያሳነሱ በማየት፤ የነበረ እና ለወደፊቱ የሚኖር የሰው ልጆች አነስተኛ ጸብ ነው፤ ደህና ሥርዐት ሲመጣ ይረጋጋል፤ ዕልቂቱን ደጋግሞ ለሕዝብ መንገር "ጥላቻን እንደማራግብ" ስለሚቆጠር ፤የባሰ ሊያመጣ ስለሚችል፤ ይልቁንስ "ዲሞክራሲ" እንዲመጣ እንታገል! እያሉ በፖለቲካ በታሰሩ የምሁራን እና የታዋቂ ግለሰቦችን ችግር እያጎሉ፤ ሕዝቡ በነሱ ብቻ እንዲወያይ እያደረጉ፤ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን በመስጠት፤ የሕዝቡን አስፈሪ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ዓይኑን አፍጥጦ እየመጣ እና ፊታቸው ላይ ተደቅኖ ቆሞ ያለውን "ሞንስተር/ሑንጉጓይ ይባላል በትግርኛ" ደንታ ሳይሰጡት፤ ኢትዮጵያ እንደ ሩዋንዳ አትሆንም፤ ሕዝቡ አንድ ሕዝብ ነው፤ ተዋልዷል፤ተዳቅሏል' ይልቁኑስ የታሰሩትን እናስፈታ እያሉ ሕዝቡን አጃጅለው ለእልቂት ዳረጉት።

ይህ የዲስተራክሽን/የአፍራሽነት ባሕሪ ተቀባይነትና ተዋናይነት ሕዝቡን አዋርነስ ኖሮት/እንዳይጠነቀቅ/ እና እራሱን ከጥቃት እንዳይከላከል ስላገደው፤ ከፍተኛ የሕሊና አጣባ ተደርጎበት ሕብረተሰቡ የገዛ አካሉ ሲቆረጥ ፤ሲታረድ፤ ሲበላ፤ ሲገደል፤ሲባረር

ዝምታን እንዲመርጥ የተጠቀሱት ክፍሎች ተዋናዮች ሆነዋል። በግልፅ እንነጋገር እንጂ! ምንድር ነው ነገሩ!

ሚዲያዎች፤ምሁራን፤ወጣቶች፤ አንዳርጋቸው ሲታሰር፤ አረቦች ኢትዮጵያዊያንን ሲያባርሩ፤ እስላማዊ ጽንፈኛ ዐረቦች፤ ክርስትያን ኢትዮጵያዊያን ሲያርዱ የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ እና መሬት አንቀጥቅጥ ጩኸትና ተቃዉሞ በአማራው ላይ ሲደርስ ግን **"ተነፍጎታል!"** ለምን? ከሩዋንዳ በባሰ መልኩ በቁጥር ብዛት የት የሌለ ግድያ ሲፈጸምበት፤ የተባባሩት መንግሥታት እንዳይሰማው፤ ዓለም እንዳይሰማው፤ ውጭ ሚዲያዎች እንዳያስተጋቡት፤ እስካሁን ድረስ ታፍኗል! ለምን ? ለዚህ ተጠያቂው ወያኔ ብቻውን ወይስ በዚህ ጽሑፍ ርዕስ ላይ የተጠቀሱት ክፍሎች? ይህ አብይ ጥያቄ ሰጥቻችኋለሁ፤ መልስ ይፈልጋል። ተወያዩበት። ይቀጥላል.......

ጌታቸው ረዳ Editor- Ethiopian Semay getachre@aol.com